An Australian Government Initiative

AUSTRALIAN multicultural foundation

SBS

## ደሜንሽያ ምንድን ነው ?

ደሜንሽያ ተፈጥሮአዊ የእርጅና አካል አይደለም፤ የአዕምሮ ህመምም አይደለም። ደሜንሽያ በአዕምሮ ላይ በደረሰ ጉዳት ሳቢያ የሚከሰት አካላዊ ህመም ነው።የተለያዩ የደሜንሽያ አይነቶች አሉ፤በጣም የተለመዱት አይነቶች የአልዛይመርስ በሽታና ቫስኩላር ደሜንሽያ ናቸው።

የደሜንሽያ ምልክቶች የማስታወስ ችሎታን ማጣት፣በተለይም የቅርብ ጊዜ ክንውኖችን ማስታወስና የስሜት መቀያየርን ያካትታል። ሰዎች በራሳቸው ላይ እየደረሰ ባለው ሁነት ኃዘን፣ፍርሃትና ንዴት ሊሰማቸው ይችላል። ተነጋግሮ የመግባባት ችግር፤ ትክክለኛ ቃላቶችን ፈልጎ የማግኘት እውክታ ሊገጥማቸው ወይም ቀስ በቀስ የመናገር፣ የማንበብና መጻፍ ችሎታቸውን ሊያጡ ይችላሉ።

ደሜንሽያ እያንዳንዱን ሰው በተለያየ ሁኔታ ስለሚያጠቃ፤በተቻለ መጠን ፈጥኖ ምርመራ ማድረግ ጠቃሚ ነው።

## ተጨማሪ መረጃ ከየት ማግኘት እችላለሁ?

ሐኪምዎ ሙሉ የአካል ምርመራ ሊያደርግልዎና የደም ምርመራ ሊያዝልዎት ይችላል። ምርመራው ከደሜንሽያ የመጀመሪያ ደረጃ ምልክቶች ጋር ተመሳሳይ የሆኑትን የመንፈስ ጭንቀት፣ የስሜት መታወክ ወይም ኢንፌክሽንን የመሰሉ የሕክምና ሁነቶች ፈልጎ ሊያገኝ ወይም አለመኖራቸውን ሊያረጋግጥ ይችላል። ሐኪምዎ የማስታወስ ችሎታዎን ሊመረምር ወይም ለተጨማሪ ምርመራ ወደ ስፔሻሊስት ዘንድ ሊመራዎ ይችላል።

በአልዛይመርስ አውስትራሊያ ስለሚቀርበው የደሜንሽያ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የሚሹ ከሆነ፤ በ 1800 100 500 ወደ ብሔራዊ ደሜንሽያ የእርዳታ መስመር መደወል ወይም www.fightdementia.org.au ድረ ገጽን ሊጎበኙ ይችላሉ። የትምህርትና የምክር አገልግሎት ድጋፍም ይሰጣሉ።

የአካባቢዎ ካውንስል ደሜንሽያ ያለባቸው ሰዎች የክብካቤ አገልግሎቶች እንዲያገኙ የሚረዳ የሥራ ድርሻ ያለው ሠራተኛ አለው። በአካባቢዎ ካለ የአረጋውያን ክብካቤ ገምጋሚ ቡድን ጋር ተገናኝተው የሚሹትን እንዲወያዩም ሁኔታዎችን ያመቻቹልዎታል።

በቋንቋዎ እንደልብዎ ተናግረው የሚሹትን መረጃና እገዛ እንዲያገኙ አስተርጓሚዎች ይዘጋጅልዎታል።

ለእርስዎና ለቤተሰብዎ መረጃ፣ እርዳታና ድጋፍ ተዘጋጅቶ አለ።ልብ ይበሉ፤ ብቻዎን አይደሉም። የሚያሳስብዎትንና የሚያስፈራዎትን ነገር ስለ ደሜንሽያ ለሚያውቅ ሰው ማካፈሉ በጣም ጠቃሚና ለመንፈስ ድጋፍ ሰጪ ነው።

---

ይህ የደሜንሽያ ማህበረሰብ ድጋፍ ልገሳ ፕሮግራም የተደጎመው በአውስትራሊያ መንግስት የጤና ጥበቃና አረጋውያን ዲፓርትሜንት ሲሆን የጎለበተው በአውስትራሊያ መድብለባህል ፋውንዴሽን ነው።(www.amf.net.au).